**የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ( ኢሕአፓ)**
Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)

ኅዳር 24/2000

## በኦጋዴን የሚካሄደው ጭፍጨፋ በአስቸኳይ ይቁም

የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ዶክተር ኮንዶሊዛ ራይስ በአዲሰ አበባ ከመለስ ዜናዊ፤ ከጅቡቲው መሪ ኦማር ገሌና ከሶማሊያ ሽግግር መንግሥት መሪዎችም ጋር ስለ አፍሪካ ቀንድ ችግር ሊዋያዩ መሆኑ ተዘግቧል። የአፍሪካ ቀንድ ችግር፥ በተለይም የሶማሊያ ችግር የተሳሳተ የአሜሪካን ፖለቲካ በሥራ ለማዋል በተሰለፈው የመለስ አገዛዝ ወረራ የተባባሰ መሆኑ የሚታወቅ ነው።

ከዚህ በተያያዘ በኦጋዴን ያለው ጦርነት ተፋፍሞ የወያኔ አገዛዝ በዚያ የሚንቀሳቀሱ ሽምቅ ተዋጊዎችን አጠፋለሁ በሚል በሰላማዊ ሕዝብ ላይ ይህ ነው የማይባል ግፍ እየፈፀመ መሆኑ ተጋልጧል። ይህን በተመለከት ዶክተር ራይስ ጉዳዩን አንስተው መለስ ዜናዊን ይወቅሱታል ተብሎ ባይጠበቅም፥ በዜጎቻችን በአጋዴን ነዋሪዎች ላይ እየደረሰ ያለውን አፈናና ግፍ በጥብቅ መቃወም ግዴታችን ነው ብሎ ኢሕአፓ ያምናል። በቦታው እየተንቀሳቀስ ያለው ድርጅት ማንነትና ምንነት በሕዝብ ላይ እየተፈፀመ ላለው ግፍ ማጠየቂያ ሊሆን አይችልም። የወያኔ ጦር ሕዝቡን በአየር እየደበደበ ፤ መንደሮችን እያጋየ፤ ሰላማዊ ሕዝብን እየገደለ ፤ ግመሎችን እየፈጀ ፤ ሕፃናትን ሳይቀር እያሳደደ ከባድ ግፍ በመፈፀም ላይ በመሆኑ ከውግዘት ሊያድነው የሚችል ምንም ምክንያት ሊኖር አይችልም። አልፎም መለስ ዜናዊና አገዛዙ ለአሜሪካ ሎሌዎች በመሆን ድጋፍን ለማግኘት ሲጥሩ በሶማሊያ ያካሄዱት ወረራ ሌላ መዘዝን እያስከተለ ከመሆኑም በላይ ለኦጋዴን ጦርነት መባባስም አንድ ሌላ ምክንያት መሆኑ የሚታይ ነው። የሀገሪቷ ኤኮኖሚ በሚያስደንቅ ሁኔታ እያደገና እየተመነደገ ነው ብሎ ችጋር ለፈጀው ሕዝብ ምፀትና ውሸት የሚናገረው የወያኔ መሪ በአሁኑ ጊዜ ሶማሊያ ተረጋግቷል ብሎ ቢቀጥፍም፥ በሶማሊያ ቀውሱና ጦርነቱ እየተባባሰና በቀን ተቀን ብዙ ወያኔ ወታደሮች እየተገደሉና እየቆሰሉ (ወደ አዲስ አበባ የጦር ኃይሎች ሆስፒታል በየቀኑ የሚመጣውን ቁስለኛ ያውም ሳንቆጥር) መሆናቸው የሚካድ አይደለም። በጣት የሚቆጠሩና አሸባሪ ናቸው በሚል ይፈለጋሉ የተባሉት ፀረ አሜሪካ ግለሰቦች ደብዛቸው ባልተገኘበትና የወረራው ማጠየቂያ መሠረተ ቢስ ሆኖ ባለበት የወያኔ ጦር በሶማሊያ ምድርም የሚያካሂደው ግድያ ለትውልድ ጥላቻን ፈጣሪ መሆኑ ግልፅ ነው።

በኦጋዴን ያለው ችግር የሚፈታው በፀረ ሕዝብ ጦረንት ሳይሆን፥ በሕዝብ እኩልነት መስፈን ነው፡፡ ይህንንም እውን ለማድርግ የወያኔ አገዛዝ መወገድ አስፈላጊ ነው ፡፡ ሁሉም የኢትዮጵያ ሕዝብ የሀገሩና የመብቱ ባለቤት ሆኖ ቢገኝ፥ ለመሰሪ ባዕዳን ቀዳዳ አይኖርም ነበር፡፡ የፀረ ሽምቅ ውጊያ አባወራ ነን ብሎን የለፈፈው የወያኔ ቁንጮ አገዛዙና የገዢው ድርጅት ወታደር የተካነው የሕዝብን ልብ ትርታ አዳምጦ ለሕዝብ ቀና ምላሽ በመስጠት ሳይሆን፥ ሕዝብን በመጨፍጨፍ ላይ መሆኑን ሊደብቅ አልቻለም፡፡ በኦጋዴን ሰብዓዊ መብት ቀን ተቀን ይጣሳል፤ ንፁህ ዜጋ ይገደላል፤ ይሰቃያል፡፡ ይህንን ኢትዮጵያውያን ሁሉ ማውገዝና መቃወም አለባቸው፡፡ በመሆኑም ኢሕአፓ ከኦጋዴን ሕዝብ ጋር አብሮ በመቆም የወያኔን አፈናና ግድያ በጥብቅ እያወገዘ በአስቸኳይም እንዲቆም ይጠራል፡፡

**EPRP**
P.O.Box 73337
Washington D.C. 20056
U.S.A
Tel. : (202) 291-4217
Fax : (202) 291-7645

**EPRP**
BP 22
Bois Colombes 92270
France

**E-mail ESPIC@aol.com** **Website: http://www.EPRP.com**